# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

## Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፡-** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት አስከ ሶሰት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ
**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

## <u>ዜና ዘገባ</u>

**መሰከረም 26 ቀን 2005 ዓ.ም**

**ኦህዴድ በግምገማ ተወጥሮ ሰነበተ፤**

**ሙስሊሙ ለወያኔ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ አስተላለፈ፤**

**ዓርብ ዕለት በአዲስ አበባ አንዋር መስጊድ ተቀውጦ ዋለ ቁጥራቸው የበዙ ሙስሊሞች ታፍሰው ታሰሩ፤**

**የወያኔ ወጣት ካድሬዎች በመለስ ቅስቀሳ ላይ ተቃውሞ አቀረቡ**

በወያኔ ምክር ቤት ውስጥ አብላጫ ወንበር ያለው ኦህዴድ የተባለው ተለጣፊ ድርጅት ካድሬዎች ባነሱት የስልጣን ይገባኛል ጥያቄ ላይ ማዕከላዊ ኮሚቴ እንዲመክርበት አስቸኩዋይ እና ዝግ ስብሰባ ማድረጉ ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ ገለጠ፡፡

ሰኞ መስከረም 21 ቀን 2005 ዓ.ም በአዳማ ከተማ አባ ገልማ አዳራሽ ውስጥ የጠቅላይ ሚኒስትር ሹመትን ተከትሎ በካድሬዎቹ በተነሳ ጥያቄ ላይ ተመርኩዞ የተጀመረው ዝግ ስብሰባ በምክትል ሊቀመንበሩ ሙክታር ከድር እና በሊቀመንበሩ አለማየሁ አቶምሳ መሪነት ሲካሄድ መሰንበቱ ታውቆዋል፡፡

በዚሁ በተደረገው ዝግ ስብሰባ ላይ ስልጣን ከሌሎች ድርጅቶች ተለይቶ ለምን ለኛ ተነፈገን.......ችሎታና ብቃት ያላቸው ምሁራኖች እያሉን ለምን የበታች እንድንሆን ተደረገ......ጠቅላይ ሚኒስትር ለመሆን መስፈርቱ ምንድነው ..... ብለው በተደጋጋሚ ግዜ የስልጣን ይገባናል ጥያቄ ያነሱ ከፍተኛ የኦህዴድ አመራሮች ላይም የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ በሚል ውሳኔ እንደተሰጠና የስልጣን ሽግሽግ እንደተደረገም ከአዳማ(ናዝሬት) የደረሰን ጥቆማ ገልጾዋል፡፡

ለብዙ ዓመታት በኦህዴድ ከፍተኛ ካድሬዎች በኩል ግዜ እየጠበቁ እና እያነሱት የሚገኘው የስልጣን ይገባናል ጥያቄ በወያኔ ቡድን ውስጥ ችግር እየፈጠረ እርስ በርስ ሲያነታርካቸው እና ሲያከራክራቸው የነበረውን ጉዳይ ለአንዴና ለመጨረሻ ግዜ እልባት ለመስጠት በሚል አስቸኩዋይ እና ዝግ ስብሰባ እንዲያደርጉ በታዘዘው መሰረት ከሰኞ መስከረም 21 ቀን ጀምሮ ለአምስት ቀናት

ባደረጉት ተከታታይ ስብሰባ ላይ ተነስቶ ብዙ ጭቅጭቅ እና ንትርክ ተደርጎበት በልዩነት ውሳኔ ማግኘቱ ታውቆዋል::

በዚሁ ውሳኔ መሰረት እስከ ዛሬ በኦህዴድ ካድሬዎች በኩል የሀገሪቱ ቁልፍ ስልጣን የሆነው የጠቅላይ ሚኒስትርነቱ ቦታ ይሰጠን የሚል ጥያቄ ቢሆንም አሁን ግን ቦታው እንደማይሰጣቸውና ወደፊትም በተሰጡዋቸው ቦታዎች ሁሉ በብቃት መምራት ብቻ እንደሚሆን ከማስጠንቀቂያ ጭምር ምላሽ እንደተሰጣቸው ተጠቁሞዋል::

ጥያቄ እያነሱ ያስቸገሩ የኦህዴድ ካድሬዎችን ለማሳመን ሲርበተበት የሰነበተው የመድረኩ መሪ ምክትል ሊቀመንበር ሙክታር ከድር በፌዴራል መንግስት አወቃቀር ውስጥ ትልቁን ድርሻ የያዝነው እኛ ነን ለአብነት ያህልም የፕሬዝዳንቱ .....የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የአፈ ጉባዔው... በምክር ቤቱ ውስጥ የመንግስት ተጠሪነቱ...የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባነቱ....የሀገሪቱ ቁልፍ የሚኒስትሮች በተለይ የገንዘብና ኢኮኖሚው ቦታዎች በእኛ የተያዙ በመሆኑ የስልጣን ጥያቄ ማንሳቱ ፋይዳ የለውም በሚል እያስፈራራና እያንጉዋጠጠ ምልስ ሲሰጥ እንደሰነበተም ከተሳታፊዎች ሾልኮ የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል::

በሙክታር ከድር መልስ የተበሳጩ ካድሬዎች በበኩላቸው እናንተ ከበረሀ ከምርኮኛነት ጀምሮ አብራችሁ የመጣችሁት ደራ ላይ ኦህዴድን ስትመሰርቱ የተነገራችሁ እና ቃል ገብታችሁ መሀላ ፈጽማችሁ የመጣችሁት ነገር ስላለ ልትፈሩና ጥያቄውን ላታነሱ ትችላላችሁ እኛ ግን አሁንም በነጻነት ያለ ጫና መስራት አለብን በማለት ተቃውሞ ማቅረባቸውን ከእነዚሁ የስብሰባው ተሳታፊዎች የደረሰን ጥቆማ አብራርቶዋል::

ወያኔ በኦህዴድ ጀርባ ታዝላ ያለች ቡድን ነች ያሉት ተሰብሳቢ ካድሬዎቹ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤትም ቢሆን አብላጫ ድምጽ ያለው ይሄው ድርጅት መሆኑን አውስተው በተለይ የድርጅቱ ማዕከላዊ ኮሚቴ አወቃቀር አግባብ ያልሆነ መሆኑን እያወቃችሁ አንድም ቀን በዚህ ጉዳይ ላይ ጥያቄ አለማነሳታችሁም የሚያሳዝን ነው ሲሉ የመድረክ መሪዎችን ተችተዋል::

አያይዘውም በዚሁ በወያኔ ውስጥ የተመሰረተው ማዕከላዊ ኮሚቴ 4 ሚሊዮን ሕዝብ ለሚወክለው ህወሀት እና 40 ሚሊዮን ሕዝብ ለሚወክለው ኦህዴድ እኩል 45 መቀመጫ መሰጠቱ የድርጅቱ የተዛባ አሰራርን አጉልቶ የሚያሳይ በመሆኑ ሊስተካከል ይገባል ሲሉም ጥያቄ ማንሳታቸው ተደምጦዋል::

በተለይ አንደኛው ስሙ ለግዜው ያልተጠቀሰ የስብሰባው ተሳታፊ ከፍተኛ ካድሬ ለ21 ዓመታት በእጅ አዙር አገዛዝ ህዝባችንን ስናስተዳድር ኖረናል አሁንም ቢሆን በህወሀቱ ገ/ተንሳይ ወ/ተንሳይ የበላይነት እየተመራን እንገኛለን ስለዚህ በዚህ ዓይነት መንገድ መቀጠል አንችልም ይሄ ማዕከላዊ ኮሚቴ ውሳኔ ሊሰጥበት ይገባል በማለት ሌላ አስተያየት መሰንዘሩም ታውቆዋል::

ኦህዴድ በዚሁ ባደረገው እልህ አስጨራሽ ዝግ ስብሰባ ላይ ከወያኔ ቡድን ትዕዛዝ ውጭ የሆነ ሀሳብ ባነሱት ካድሬዎች ላይ መስፈርት ያለው እርምጃ እንደሚወሰድ በይፋ የተነገራቸው ሲሆን በተለይ

ወጣት የሆኑ ከተማ አመጣሽ ካድሬዎች ላይ ከረር እና መረር ያለ እርምጃ እንደሚወሰድባቸው በይፋ ተነግሮዋቸዋል::

የካድሬዎቹን አግባብ ያለው ጥያቄ መልስ መስጠት ያቃታቸው የወያኔ ቡድን ተላላኪ የሆኑት የድርጅቱ አመራሮች አለማየሁ አቶምሳ እና ሙክታር ከድር የአመለካከት ችግር ባለባችሁና የአመራር ውስንነት ባሳያችሁት ላይ እርምጃ እንወስዳለን......አዲስ ምደባም እናወጣለን በማለት ሲያስፈራሩዋቸው እንደነበር ከስብሰባው ተሳታፊዎች ሾልኮ የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል::

እነ አለማየሁ እንዳሉት ከሆነ ኦህዴድ ለአንዴና መጨረሻ ግዜ አደረኩት ባለው የሰላና መደባዊ ግምገማ ሶስት አይነት እርምጃ እንደሚወስድ የገለጸ ሲሆን እነሱም የማያዳግም እርምጃ የሚወሰድባቸው.....በይቅርታ የሚታለፉና የቦታ ዝውውር የሚሰጣቸው መሆኑን እነዚሁ ወገኖች አጋልጠዋል::

ወያኔን የስንግ ይዘው አላላውስ ያሉትን ካድሬዎች የማያዳግም እርምጃ የሚወሰድባቸው ተብለው በሙስና ሰበብ ክስ ተመስርቶባቸው ወደ ዘብጥያ ሊያወርዱዋቸው መሆኑን ተሰብሳቢዎቹ አጋልጠዋል::

የኦሮሞን ህዝብ ጥቅም አሳልፈን አንሰጥም...... ከአብራኩ የወጣነው ልጆቹ ከመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር አብሮ በመተሳሰብ እና በጋራ መኖር መርህ ላይ ተመስርቶ ቢሆንም አሁን ያለው የወያኔ አመራር ሂደት ግን ኦሮሞው እየተጨቆነና የስልጣን ባለቤት እንዳይሆን ሆን ተብሎ እየሰራ በመሆኑ እንዲስተካከል ይህን...... በማለታችን ደግሞ የሚያስከፍችሁ ከሆነ የሚመጣውን መስዋዕትነት ሁሉ እንቀበላለን ሲሉም ጥቂት የኦህዴድ ካድሬዎች በንዴት ሲገልጹ እንደነበረም ተጠቁሞዋል::

የካድሬዎቹ መልስ እና ንግግር ያበሳጫቸው የመድረኩ መሪዎች ኦህዴድ በእንዲህ ያለ የተዝረከረከና የተጨማለቀ አሰራር ሊቀጥል አይችልም..... የእናት ድርጅቱን(ወያኔን) ህልውና ለማስቀጠል ሲባል ለአንዴና ለመጨረሻ ግዜ ውሳኔ የሚሰጥበት ይሆናል በማለት ዛቻ አዘል አጸፋዊ መልስ ሰጥተዋል::

የኦህዴድ ካድሬዎች ከሌሎቹ አቻ የወያኔ ሶስት ድርጅት ካድሬዎች ተነጥለው በተለየ ግምገማ ሊጠመዱ የቻሉበት ዋነኛው ምክንያት የጠቅላይ ሚኒስትርነቱ ቦታ ይገባናል የሚለው ጥያቄን በማንሳታቸውና በማራገባቸው የተነሳ እንደሆነም ከውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ጥቆማ ለማረጋገጥ ተችሎዋል::

በተደረገው ግምገማ ወጥ አቋዋም ይዘው እስከ መጨረሻው ድረስ የተከራከሩትን ከፍተኛ የዲስፐሊን ግድፈት በሚል በሙስና ሰበብ ተጠያቂ እንዲሆኑ...... ሌሎች የሚዋልሉትን ደግሞ በከባድ ይቅርታ እንዲታለፉና ወደ ቀድሞ ቦታቸው እንዲመለሱ ሲደረጉ በዝምታ ተውጠው አንዳችም ተቃውሞ ሳያሰሙ የነበሩት የቦታ ሽግሽግ በሚል እድገት እንደሚሰጣቸው ከዚሁ የስብሰባ ተሳታፊዎች ሾልኮ የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል::

በተያያዘ ዜና በአንድ ወቅት የክልሉ ፕሬዝዳንት የነበረውና የአሁኑ የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስትር በሆነው ጁኔዲ ሳዶ ላይ የቀረበው አጀንዳ አንዱ ሲሆን በዚህ ዙሪያም ያለውን ሁኔታ መጀመሪያ እራሱ ለተሰብሳቢዎቹ ገለጻ እንዲያደርግና እንዲያስረዳ መደረጉንም ከተሰብሳቢዎቹ የሾለከው ጥቆማ አስረድቶዋል::

ከሳዑዲ አረቢያ ኤምባሲ ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንደነበረውና ገንዘብም በተለያዩ ግዜያት እየወሰደ እንደነበር ተደርሶበት ባለቤቱ ለእስር የተዳረገችበት የወያኔው ከፍተኛ ካድሬ ጁኔዲ ሳዶ ላይ የኦህዴድ ማእከላዊ ኮሚቴ ጉዳዩን መርምሮ ውሳኔ እንዲሰጥበት ከነበረከት ስምኦን በኩል ትዕዛዝ በመተላለፉ በዚህ ግምገማ ላይ አንዱ አጀንዳ ሆኖ ቀርቦ እንደነበር ተጠቁሞዋል::

ጉዳዩን እንዲያስረዳ እድል ተሰጥቶት የነበረው ይሄው የወያኔ ከፍተኛ ካድሬ እንዳለው ከሆነ ከምንም አይነት የእስልምና አክራሪ ድርጅት ጋር ግንኙነት እንደሌለኝ ቤቱ እንዲያውቅልኝ ካለ በሁዋላ ገንዘቡን ከሳዑዲ አረቢያ ኤምባሲ ልንወስድ የቻልነውም ከሁለት ዓመት በፊት በተወለድኩበት ቀዬ ያስጀመርኩትን መስጊድ ለማሰራት ነው ሲል ጠቅሶ በአሁኑ ሰዓት ባለቤቲ የልጆቼ እናት በማዕከላዊ እስር ቤት ውስጥ እየተሰቃየች ትገኛለች እኔም ቢሆን በደህንነት ክትትል ውስጥ እገኛለሁ በማለት አብራርቶዋል::

ተሰብሳቢዎቹ በበኩላቸው አንተ የድርጅት ከፍተኛ ካድሬ እና የመንግስት ከፍተኛ ባለስልጣን ሆነህ በራስህ ፈቃድ ከኤምባሲዎች ጋር ግንኙነት መፍጠርህ ድርጅቱ ከሚያራምድበት ዓላማ ጋር ፈጽሞ የሚቃረን በመሆኑ ተጠያቂ ልትሆን የገባህል ከዚህም በላይ ባለቤቲ ታሰረች ብለህም በተለያዩ ጋዜጦች ላይ ዝርዝር መግለጫ ጽፈህ መስጠትህ ከባድ ወንጀል በመሆኑ ኮሚቲ ተቂዋቂሞ ውሳኔ ሊሰጥህ ይገባል በሚል እንደተነገረው ይሄው ሾልኮ የደረሰን ጥቆማ አብራርቶዋል::

በቅርቡ በሀገር ውስጥ የሙስሊሙ ህዝብ ካነሳው የመብት ጥያቄ ጋርም በተያያዘ ውስጣዊ ድጋፍ የሚሰጡ የመንግስት ከፍተኛ ባለስልጣናት መሀከል አንዱ ጁኔዲ ሳዶ ነው በሚል በደህንነት ልዩ ክትትል ሲደረግበት እንደነበረም ለጋዜጦች በበተነው ደብዳቤ መግለጹ አይዘነጋም::

ይህ በእንዲህ እንዳለ ከመስከረም 27 ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ ለሚደረገው አዲስ የሙስሊም አመራሮች ምርጫ አስመራጭ ኮሚቲ ተሰየመ ተብሎ መገለጹ ሙስሊሙን ህዝብ የማይወክሉና ያልመረጣቸው ናቸው በሚል በየስፍራው ተቃውሞ መቀስቀሱ ታወቀ::

የኢትዮጵያ የእስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት (መጅሊስ) ምርጫ ከመስከረም መጨረሻ ጀምሮ እስከ ጥቅምት ወር መጨረሻ ድረስ ለማካሄድ ምርጫውን ለመታዘብና ለመቆጣጠር የሚችሉ ናቸው ተብለው የወያኔ ደጋፊና ካድሬዎች በእጅ ማውጣት ተመረጡ በሚል ይፋ በመደረጉ ህዝበ ሙስሊሙ ቁጣውን እየገለጸ መሆኑ ታውቆዋል::

እስከ ጥቅምት 20 ቀን 2005 ዓ.ም ድረስ በየሳምንቱ ተከታታይ በቀበሌ እና በየትምህርት ቤቶች ግቢ ውስጥ ለሚደረገው የመጅሊስ ምርጫ አስመራጭ ናቸው የተባሉት ቀድሞ ከነበረው አመራር ጋር አብረው ሲሰሩና በጥቅም የተሳሰሩ መሆናቸውን በማጋለጥ ሙስለሙ ተቃውሞ እያሰማ ይገኛል::

ሰሞኑን ተደረገ ተብሎ ለአስመራጭ ኮሚቴነት የተሾሙት የቀድሞው የፈረሰው መጅሊስ ያዘጋጃቸው ሲሆን በምርጫውም የቀድሞዎቹን በቦታቸው ለመመለስ የሚደረግ ሻጥር መሆኑንም ሙስሊሙ በከፍተኛ ተቃውሞ ቁጣውን እየገለጸ ነው።

ዓርብ መስከረም 25 ቀን 2005 ዓ.ም በአዲስ አበባና በተለያዩ ከተሞች በተቀሰቀሰው ተቃውሞ ወያኔ ጥያቄያችንን ሊያደመጥ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ከእንግዲህ ለሚወሰደው እርምጃ ሁሉ ተጠያቂው እሱ ነው በማለት ሙስሊሙ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ማስተላለፉን ከተለያዩ ከተሞች የደረሰን ጥቆማ ገለጸ።

በአዲስ አበባ በታላቁ አንዋር መስጊድ የስግደት ፕሮግራማቸውን ከጨረሱ በሁዋላ እንደተለመደው ግዜ ሁሉ አፋቸውን በመያዝ እና ነጭ መሀረብ እያውለበለቡ በዝምታ ተቃውሞዋቸውን ያሳያሉ ተብሎ ሲጠበቅ ሳይታሰብ ድንገት ሁሉም በያለበት ቆሞ በከፍተኛ ድምጽ ቢጫ ወረቀት በማውጣት እጃቸውን ወደ ላይ ከፍ አድርገው «**ድምጻችን ይከበር!...የታሰሩ መሪዎቻችን በአስቸኩዋይ ይፈቱ!...ጥያቄያችን መልስ ካላገኘ ምርጫውን አናካሂድም!....ወያኔ የሰላም ጸር ነው!...**» የሚሉና ሌሎችን መፈክሮች ሲያስተጋቡ ውለዋል።

በዚሁ ተቃውሞ ላይ ሴት ወንድ ....ወጣት ሽማግሌ....ህጻን አሮጊት..... ነጋዴ ባለሀብት .....ሳይል ሁሉም በአንዋር መስጊድ ግቢና ዙሪያውን በመሆን ለወያኔ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ የሚሆን ቢጫ ወረቀት በመያዝ እያውለበለቡ በከፍተኛ ድምጽ ተቃውሞዋቸውን ሲያሰሙ የዋሉ ሲሆን የወያኔ ፌዴራል ፖሊስም ቁጥራቸው ቀላል ያልሆኑ ሙስሊሞችን አፍሶ በፓትሮል እየጫነ ሲወስዳቸው ታይቶዋል።

ከወትሮው በተለየ መልኩ ቢጫ ወረቀት አዘጋጅተው እያውለበለቡ ተቃውሞዋቸውን ያሰሙበትን ምክንያት በስፍራው ከነበሩ ሰዎች ለመረዳት እንደተቻለው ከሆነ ወያኔ ለጠየቅነው አግባብ የሆኑ ጥያቄዎች በቂ መልስ ከመስጠት ይልቅ ነገሮች ሁሉ ወዳልተፈለገ አቅጣጫ እንዲያመሩና እንዲንሻፈፉ እያደረገ በመሆኑ.....እንዲሁም  እሁድ መስከረም 27 ቀን 2005 ዓ.ም የሚጀመረውን ምርጫ ያስቀመጥናቸው ጥያቄዎች ሳይመለሱ እንዳከናወን ለማሳሰብና ይህን ተከትሎ አደጋ ቢፈጠር ተጠያቂው ወያኔና የወያኔ ባለስልጣናት ብቻ መሆናቸውን ለመሳየትና ለማስጠንቀቅ ነው ብለዋል።

መቶ ሺህ የሚሆን ቁጥር ያለው የሙስሊም እምነት ተከታዮች ተገኝተዋል ተብሎ በሚገመትበት በዚህ በታላቁ አንዋር መስገድ ተቃውሞ ላይ የውጭ ሀገር ዓለም አቀፍ ሚዲያዎች ተገኝተው እንቅስቃሴውን ሲቀርጹና ሲያነጋግሩ የተስተዋለ ሲሆን በተለይ የተቃውሞው መጨረሻ አካባቢ የወያኔ ፌዴራል ፖሊስ ልዩ መቺ ኃይል የተባለው ቁጥራቸው የበዙ ሙስሊሞችን አፍሶ ወዳልታወቀ ስፍራ ከመውሰዱም በተጨማሪ በሺህዎች የሚቆጠሩ የፌዴራል ፖሊሶች በአንዋር መስጊድ ዙሪያ ከጎጃም በረንዳ እስከ ጣና ገበያ....ከተክለሀይማኖት እስከ ቢስ መብራት ድረስ ዙሪያውን ወጥሮ እንደነበርም ለማየት ተችሎዋል።

በአሁኑ ሰዓት የሙስሊሙ ተቃውሞ እየጠነከረና እየጠጠረ የመጣ መሆኑን ወያኔዎችም በግዜ ነቅተው የሙስሊሙን ህዝብ ጥያቄ አክብረው በቂ መልስ እንዲሰጡበት የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ በቢጫ ካርድ የሰጡ ከመሆኑም በላይ ወያኔ ቀይ መስመሩን ሊያልፍ ጥቂት እንደቀረውና ይሄንን ካለፈ ለሚፈጠረው ችግር ሁሉ ተጠያቂው እነሱ መሆናቸውን ለማሳየት እና ብዙ ግዜ ፋውል እየሰሩ በመሆናቸው በግዜ የእርምት እርምጃ እንዲወስዱ ለማስገንዘብ የተደረገ ታላቅ ተቃውሞ መሆኑን በስፍራው ከነበሩ ተሳታፊዎች የተገኘው ጥቆማ ያስረዳል።

ሙስሊሙ አቋዋም ወስዶ የጠየቅነው ጥያቄ መልስ ካላገኘና የታሰሩት ካልተፈቱ ምርጫውን አናካሂድም ምዝገባም አናደርግም በማለቱ የተደናገጡት የወያኔ ቡድን ባለስልጣናት በቤት ቁጥር እየዞሩ ቤት ለቤት እያስፈራሩ ምዝገባ ለማድረግ ሙከራ ቢያደርጉም ያልተሳካላቸው በመሆኑ ከፍተኛ ኪሳራ ውስጥ መውደቃቸውን ተዘዋዋሪ ዘጋቢያችን በተለያዩ ሰፈሮች ተዘዋውሮ ካገኘው መረጃ ለመረዳት ተችሎዋል።

እሁድ በሚጀመረው ምርጫ ከወያኔ ጋር የቀረበ ግንኙነት ያላቸውና የወያኔን ጉዳይ የሚያስፈጽሙ ሰዎች ቦታው ሊሰጣቸው እንደሆነ የሚናገረው ሙስሊሙ ህብረተሰብ በተለይ ለዚሁ ምርጫ ሲባል ውጭ ሀገር ድረስ ተልከው በመንግስት ወጪ ተምረው የመጡና አልአበሽ የተሰኘውን አስተምህሮ ሊያስፋፉ የሚችሉ ሙስሊሞች እንዲመረጡ ከወዲሁ ዝግጅቱ መጠናቀቁን ተረጋግጦዋል ሲሉም ይናገራሉ።

ከዓመት በፊት ወደ ሊባኖስ ተልከው በመጅሊሱ ወጪ ስልጠናና ትምህርት ሲከታተሉ የቆዩትና ለአሁኑ ምርጫ እጩ ሆነው የቀረቡት የወያኔ አባል እና ደጋፊዎች ተመርጠው መጅሊሱን እንዲቆጣጠሩላቸው የቀድሞው መጅሊስ አባላት እና ቅርበት ያላቸው ሰዎች በአስመራጭነት ተመልሰው እንዲቀመጡ መደረጋቸውን ተከትሎ ህዝበ ሙስሊሙ በመቃወሙ ሰሞኑን በአዲስ አበባ በተለያዩ መሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ ታዋቂ የሙስሊሙ ሰዎችን ሰብስበው ሲያስጠነቅቁዋቸው እንደነበር ታውቆዋል።

በአዲስ አበባ ባህል አዳራሽ ውስጥ በተደረገው ስብሰባ ላይ የአዲስ አበባ ከንቲባ ኩማ ደመቅሳ ሙስሊሙ ምርጫውን እበጠብጣለሁ ብሎ ችግር ቢፈጥር ለሚደርስበት አደጋ ሁሉ ተጠያቂው እራሱ መሆኑን ልትነግሩት ይገባል የሚል እብሪት አዘል ንግግር በመናገሩ ሙስሊሙ ይበልጥ እንደተበሳጨ ከተሰብሳቢዎቹ የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል።

ጥቂት የወያኔ ደጋፊና የስርዓቱ ተጠቃሚ የሆኑ የሙስሊም ነጋዴዎች በዚሁ ስብሰባ ላይ ተገኝተው ያደረጉትን ንግግር በመደጋገም በቴሌቪዥን እያሰራጩ ከመክረማቸውም በተጨማሪ አስመራጭ ተብለው የተሰየሙት በዲሞክራሲያዊ ምርጫ አሸንፈው የመጡ በመሆናቸው ሁሉም ሙስሊም እንዲቀበላቸው እያሉ ሲማጸኑ ተደምጠዋል።

የታሰሩት የመስሊሙ ተወካዮች ሳይፈቱ የሚደረገው ምርጫ የማስመሰያና የማንቀበለው ነው በማለት ተቃውሞ እያሰሙ ያሉትን ሙስሊሞች የአክራሪ ቡድን

አባሎች ናቸው እያሉ እያስፈራሩዋቸው ከመሆኑም በላይ አንዳንዶቹን ምርጫው እስኪጠናቀቅ ድረስ ወዳልታወቀ ስፍራ በስውር እያፈኑ እየወሰዱዋቸው መሆኑም ታውቆዋል።

በሙስሊሙ ህዝብ የተመረጡት እና በእስር ላይ የሚገኙት 17 የሙስሊሙ ተወካዮች ወደፊትም ይመሩናል ተፈትተው ምርጫ ውስጥ ይግቡ የሚል ጥያቄ ቢያነሱም ሰሚ እና አድመጭ በማጣታቸው አብዛኛው ሙስሊም በምርጫው ላለመሳተፍ መወሰኑንም ተዘዋውሮ ያነጋገራቸው ዘጋቢያችን ገልጾዋል።

በህጋዊ መንገድ በተደረገ ምርጫ ሙስሊሙ አምኖበት...... የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒሲቲር አውቆት የተመረጡትን መሪዎቻችንን የወያኔ ደጋፊ ወይም አባል አይደላችሁም በሚል ለእስር ዳርጎ ቢያሰቃያቸውም እኛም በዚህ ምርጫ ድምጽ አንሰጥም...... በምርጫውም አንሳተፍም በማለት የጠራ አቁዋም መያዛቸውን ተዘዋዋሪ ዘጋቢያችን አስረድቶዋል።

ምርጫው ወጣለት በተባለው ፕሮግራም መሰረት ከመስከረም 27 ቀን 2005 ዓ.ም እስከ ጥቅምት 20 ቀን 2005 ዓ.ም ድረስ የቀበሌ፤የወረዳ፤የዞን ፤የክፍለ ከተማ ፤የክልል እና የፌዴራል አመራሮች ምርጫ እንደሚደረግ ቢወሰንም ሙስሊሙ ህዝብ ግን በመበሳጨቱ በምርጫው እንደማይሳተፍ ከወዲሁ እየተነገረ ይገኛል ሲልም ተዘዋዋሪ ዘጋቢያችን ገልጾዋል።

ከወራት በፊት ጀምሮ በወያኔ ላይ ተቃውሞ ሲያስተጋባ የነበረው ሙስሊሙ ህብረተሰብ አሁንም እንደቀጠለበት መሆኑን ተዘዋዋሪ ዘጋቢያችን ያገኘውን መረጃ ዋቢ በማድረግ ገልፆዋል።

በታላቁ አንዋር መስጊድ .....በአወሊያ ትምህርት ቤት እና በተለያዩ መስገዶች ሙስሊሙ በተለያየ መንገድ ተቃውሞውን ሲያስተጋባ የነበረ ሲሆን ሰሞኑን ይህንኑ ተቃውሞ አልጀዚራ የተሰኘው ዓለም አቀፍ ሚዲያ በምስል አስደግፎ በማሰራጨቱ በወያኔ ቡድን ውስጥ ከፍተኛ መደናገጥ መፈጠሩ ታውቆዋል።

ባለፈው ሳምንት እና ከዛም በፊት በታላቁ አንዋር መስጊድ የተገኙት የሙስሊሙ እምነት ተከታዮች በሰላማዊ መንገድ አፋቸውን በእጃቸው በመያዝ እና ነጭ መሀረብ በማውለብለብ ለ2 ሰዓታት ተቃውሞ ሲያሰሙ የነበረውን ትዕይንት አልጀዚራ ደጋግሞ ለእይታ በመልቀቁና ለዓለም ህብረተሰብ በማጋለጡ የወያኔ ቡድን ባለስልጣናት ክፉኛ ከመበሳጨታቸውም በተጨማሪ እርስ በርስ ሲያነታርካቸው እንደነበረም ታውቆዋል።

እሁድ መስከረም 27 ቀን 2005 ዓ.ም በተጀመረው ምርጫ ላይ አደጋ ሊፈጠር ይችላል በሚል በሀሰት ህዝበ ሙስሊሙን ስጋት ውስጥ እንዲወድቅ እያደረጉት ያሉት የደህንነት ሰዎች ምርጫው ከመጀመሩ በፊት በፍተሻ እና በውጠራ ጭንቀት ውስጥ እየከተቱት መሆኑ ታይቶዋል።

የወያኔ ቡድን ከሙስሊሙ ህዝብ ከፍተኛ ተቃውሞ የገጠመው ከመሆኑም በላይ ከእንግዲህ ላይታረቅ ቅራኔ ውስጥ የገባ በመሆኑ ይህንን ጥያቄ ወደ ሌላ ለመቀየር እና ለማዞር ሲል ከተቀሩት የክርስትና እምነት ተከታይ ወገኖቹ ጋር ሊያጋጭ ውስጥ ውስጡን በብሔራዊ መረጃና ደህንነት ቢሮ እየተዶለተ መሆኑንም የውስጥ አዋቂ ምንጮች ጥቆማ አጋልጦዋል።

በምርጫው ወቅት  ሙስሊሙ ችግር ቢፈጥር በሚል በምስጢር ልዩ መቺ ኃይል መዘጋጀቱን የውስጥ አዋቂ ምንጮች ጠቁመው ችግሩን የሚፈጥሩት የወያኔ የደህንነት እና መረጃ ሰዎች እንጂ ሙስሊሙ እንደማይሆን እየተነገረም ይገኛል::

በመጨረሻም በቅርቡ የወያኔ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆኖ የተሾመው የደቡቡ ክልሉ የወላይታ ተወላጁ ኃይለማርያም ደሳለኝ  የተረከበው ስልጣን የይስሙላ እንደሆነ በስፋት ህዝቡ እየተናገረ ይገኛል::

ስልጠኑን ተረክቦ ቃለ መሀላ በፈጸመ በሰዓታት ውስጥ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ስብሰባ ላይ ለመገኘት ወደ አሜሪካ ኒውዮርክ ያቀናው ይሄው ግለሰብ ከፍተኛ ተቃውሞ እንዳጋጠመውም ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል::

ግለሰቡ የተማረ በመሆኑ በራሱ መንገድ የተወሰነ ርቀት ይጉዋዛል ተብሎ ተስፋ ተጥሎበት የነበረ ቢሆንም እንደጋሪ ፈረስ መለስ ዜናዊ በሙት መንፈሱ እየመራውና ከእሱ አስተሳሰብ  ብሎም እቅድ ውጭ እንደማይንቀሳቀስ በመግለጹ በኒውዮርኩ ስብሰባ ላይ ተቃውሞ እንዳጋጠመው ለማወቅ ተችሎዋል::

የመለስን ሌጋሲ እናስፈጽማለን እያለ ባገኘው መድረክ ሁሉ እየወተወተ ያለው ይሄው ኃይለማርያም በወያኔ ቡድን ውስጥ ያለውን የስልጣን ይገባናል ሽኩቻ ለማርገቢያ ተጠቀሙበት እንጂ በራሱ መንገድ እና እቅድ የማይመራ መሆኑ ከወዲሁ የተረጋገጠ ከመሆኑም በላይ አሁንም ስልጣኑ ሙሉ ለሙሉ በህወሀት እጅ መሆኑን ህዝቡ እየተናገረ ነው::

በተለይ ይላሉ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች በተለይ መለስ በራሱ መንገድ ሲጉዋዝባቸው የነበሩት ኢ ዲሞክራሲያዊ መንገዶች  እንዳሉ ሳይስተካከሉና ሳይታረሙ ባሉበት ሁኔታ የመለስን ራዕይ እናስፈጽማለን እያለ መናገሩ ግለሰቡ በራሱ የማይተማመንና እንደ ጋሪ ፈረስ የሚመራ ብሎም አንዳችም የመወሰን ስልጣን እንደሌለውና በህወሀቶች የሚሽከረከር ሮቦት መሆኑን ያሳያል ያሉት እነዚሁ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ከአንድ ጤነኛ አዕምሮ ካለው ሰው የማይጠበቅ ነው ሲሉም በንዴት ይገልጻሉ::

ምንም እንኩዋን እነ ኃይለማርያም ደሳለኝ በመለስ ሙት መንፈስ እየተነፈሱ ቢሆንም ወጣቱ የወያኔ  ካድሬ ግን ተቃውሞ እያሰማ ለመለስ ዜናዊ እየተሰራ ያለው ለከት የለሽ ፕሮፓጋንዳ በአስቸኩዋይ እንዲቆም መጠየቃቸው ታውቆዋል::

የወያኔ መሪ የነበረው መለስ ዜናዊ ከሞተም በሁዋላ በሚዲያ እየተሰራለት ያለው ቅስቀሳና ፕሮፓጋንዳ እጅግ የተጋነነ እና ተዓማኒነት የጎደለው በመሆኑ በአስቸኩዋይ እንዲቆምና አቅጣጫው እንዲቀየር ሲሉ ወጣት ካድሬዎቹ ተቃውሞ ማቅረባቸው ተነግሮዋል::

ሰሞኑን በአዲስ አበባ ከተማ በአንድ የስብሰባ አዳራሽ ውስጥ የወያኔ ወጣት ከፍተኛ  ካድሬዎች ባደረጉት ስብሰባ ላይ የመለስ ስም ገንኖ ከመውጣቱም በላይ እኛ በድርጅቱ ውስጥ ሚና የሌለን የሚያስመስል የተጋነነ ፕሮፓጋንዳ መሰራጨቱ ተገቢ ባለመሆኑ ከእንግዲህ ሊቆም ይገባል የሚል

መልእክት በማስተላለፋቸው በውስጣዊ ችግር ተተብትቦ ያለው የወያኔ ቡደን በረሀ አመጣሽ ሰዎች ክፉኛ በመደናገጥ ስብሰባው ለሌላ ግዜ እንዲተላለፍ ማድረጋቸው ታውቆዋል፡፡

በአሁኑ ሰዓት አዲስ የተሾመውን ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝን ጨምሮ ሌሎችም ባለስልጣናት ከሞተም በሁዋላ በመለስ ሳንባ የሚተነፍሱ የሚመስሉ ሁሉ አላስፈላጊ ውደሳና ቅጥ ያጣ ቅስቀሳ ማድረጋቸው ለድርጅቱም ኪሳራና ውድቀት እንጂ ትርፍ አይደለም ያሉት ወጣት ካድሬዎቹ የመለስ ራዕይ ተብሎ የሚናፈሰው የአባይ ግድብ ቀድሞም የነበረ መሆኑ እየታወቀ የአንድ ግለሰብ እቅድ አስመስላችሁ ማቅረባችሁ ድርጅቱንና እኛንም ማሳነስ ነው ሲሉ ተቃውሞ በመግለጻቸው ለሌላ ግዜ ስብሰባው እንዲተላለፍ መደረጉን የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል፡፡